በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

የመ.ቁ.229489

ጥር 22/2015 ዓ.ም

ዳኞች፡ ተፈሪ ገብሩ(ዶ/ር)

እንደሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነፃነት ተገኝ

አመልካች፡ አቶ ተሰማ አያሌው ከጠበቃ አቶ ገበየሁ ይርዳው ጋር ቀርበዋል

ተጠሪ፡ ወ/ሮ ፀሐይነሽ ዘለቀ፡- አልቀረቡም

መዝገቡ ተመርምሮ ተከታዩ ፍርድ ተሰጥቷል፡፡

ፍ ር ድ

ጉዳዩ ጋብቻ የተፈፀመበትን ቀን አስምልክቶ በባልና ሚስት መካከል የቀረበ ክርክርን የሚመለከት ነው፡፡ የሰበር አቤቱታው የቀረበው የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/216111 ላይ መጋቢት 20/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን በማጽናት የሰጠውን ትዕዛዝ በመቃወም ነው፡፡

ክርክሩ የተጀመረው የአሁን ተጠሪ በፌዴራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአሁን አመልካች ላይ ባቀረቡት ክስ ነው፡፡ የክሱ ጭብጥ ከአሁን አመልካች ጋር በባህላዊ መንገድ ግንቦት 07/2007 ዓ.ም

ማ ሳታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የፈፀሙት ጋብቻ በፍርድ ቤት ውሳኔ ቀሪ ሆኖ የጋራ ንብረት ክፍፍል እንዲደረግ ዳኝነት የሚጠይቅ ነው፡፡

አመልካች ለዚሁ ክስ በሰጡት መልስ ፍቺ እና የፍቺ ውጤት በአንድነት ሊቀርብ አይገባም፤ ጋብቻ የተፈፀመውም በክሱ ውስጥ በተጠቀሰው ጊዜ ሳይሆን ግንቦት ወር 2009 ዓ.ም ውስጥ ነው የሚል እና በንብረት ክፍፍሉ ላይም አለኝ ያሉትን ነጥቦች በማቅረብ ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍርድ ቤትም የግራ ቀኙን ክርክር እና ማስረጃን ከመረመረ በኋላ ጋብቻው የተፈፀመው በ2007ም ሆነ በ2009 ዓ.ም ለመሆኑ በቀረቡት ማስረጃዎች አልተረጋገጠም፤ ይልቁም የቀረቡት የሰው ምስክሮች ግራ ቀኙ ከ2008 ዓ.ም ጀምሮ በጋብቻ አብረው ሲኖሩ የነበረ ለመሆኑ የትዳር ሁኔታን በማስረዳት ያረጋገጡ በመሆኑ ጋብቻው የተፈፀመው በ2008 ዓም ነው በማለት ይህንኑ በውሳኔ ቀሪ አድርጓል፡፡

በአሁን ተጠሪ ይግባኝ ባይነት ይህንኑ ውሳኔ በይግባኝ የተመለከተው የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የግራ ቀኙ ጋብቻ የተፈፀመው ግንቦት 2007 ዓ.ም ለመሆኑ በዚሁ ቀን የተፈረመው የጋብቻ ውል ሰንድ የቀረበ ሲሆን የአሁን አመልካች ይህንን ማስረጃ ሊያስተባብል የሚችል ማስረጃ አለማቅረባቸውን ጠቅሶ የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን ውድቅ በማድረግ ጋብቻው የተፈፀመው ግንቦት 2007 ዓ.ም ነው በሚል ይህንኑ በውሳኔ ቀሪ አድርጓል፡፡ አመልካች ይህን ውሳኔ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀረቡት የይግባኝ አቤቱታ በትዕዛዝ ተሰርዟል፡፡

የአሁን የሰበር አቤቱታ የቀረበው በዚሁ ጉዳይ ላይ ነው፡፡ አመልካች ሰኔ 20/2014 ዓ.ም በተፃፈ የሰበር አቤቱታ በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ በተሰጠው ውሳኔ እና ትዕዛዝ ላይ ተፈፅሟል ያሉትን መሰረታዊ የህግ ስህተት ጠቅሰው በዚህ ችሎት እንዲታረምላቸው ጠይቀዋል፡፡ የቀረበው የሰበር አቤቱታ ተመርምሮ አመልካች የጋብቻ ውሉን የሚያስተባብል ማስረጃ አላቀረበቡም በሚል ምክንያት ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የስር ፍርድ ቤት ውሳኔን የሻረበት አግባብ ከጋብቻ ውል ህጋዊነት አንፃር በዚህ ችሎት እንዲመረመር በመታዘዙ ግራ ቀኙ በፅሁፍ እንዲከራከሩ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ እና መሰረታዊ የክርክሩ ይዘት በአጭሩ ከላይ የተመለከተውን ሲመስል ችሎቱም በሰበር አጣሪው ችሎት ሊጣራ ይገበዋል ተብሎ በተያዘው ነጥብ ሳይወሰን የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው የስር ፍርድ ቤቶች ውሳኔ እና ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ሕጎች ጋር በማገናዘብ መርምሯል፡፡

ከክርክሩ ይዘት በግልፅ መገንዘብ እንደሚቻለው ግራ ቀኙን እስከዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ድረስ እያከራከረ ያለው ጋብቻቸው የተፈፀመበትን ቀን እንጂ በመካከላቸው ጋብቻ የመኖሩ ጉዳይ አይደለም፡፡ ጋብቻ መኖሩ ካልተካደ በመካከላቸው ጋብቻው መቼ ተፈፀመ የሚለው በማስረጃ ሊረጋገጥ የሚችል የፍሬ ነገር ክርክር ይሆናል፡፡ በመሰረቱ አንድ ጋብቻ የተፈፀመበትን ሥርዓት፣ ቀንና ቦታ እንዲሁም የተመዘገበበት ቀን የሚታወቀው አግባብ ባለው አካል በሚሰጠው የጋብቻ ምስክር ወረቀት እንደሆነ የተሻሻለው የቤተሰብ ህግ አዋጅ ቁጥር 213/1992 አንቀፅ 30/3/ ይደነግጋል፡፡ ጋብቻ ስለመኖሩ ባከራከረ ጊዜም የጋብቻው መፈፀሙን ለማስረዳት የሚቻለው ጋብቻው በተፈፀመበት እለት ወይም ከዚያ በኋላ በህጉ አግባብ ተዘጋጅቶ የተሰጠን የጋብቻ ምስክር ወረቀት በማቅረብ ስለመሆኑ የቤተሰብ ህጉ አንቀፅ 94 ይደነግጋል፡፡ ሆኖም ጋብቻ መኖሩ ሳይካድ

የተፈፀመበት ቀን ላይ ብቻ ክርክር በተነሳ ጊዜ ፍሬ ነገሩ ሊረጋገጥ የሚገባበትን የማስረጃ ዓይነት አስምልክቶ በህግ ተለይቶ የተመለከተ ነገር ባለመኖሩ በማናቸውም ማስረጃ ማረጋገጥ የሚቻል ነው፡፡

አሁን በቀረበው ጉዳይ በግራ ቀኙ መካከል ጋብቻ ስለመኖሩ ያልተካካዱ ቢሆንም በሁለቱም ወገን በአስረጂነት የቀረበ የጋብቻ ምስክር ወረቀት የለም፡፡ በአንፃሩ ተጠሪ ጋብቻ መኖሩን ለማረጋገጥ በማስረጃነት ያቀረቡት በጋብቻው ቀን ተፈርሟል ያሉትን የጋብቻ ውል ነው፡፡ ከዚህ አንፃር ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቱ በግራ ቀኙ የቀረቡትን ማስረጃዎች ዓይነት እና ይዘት ከመረመረ በኋላ ተጠሪ ያቀረቡት የሰነድ ማስረጃ ፍሬ ነገሩን በተሻለ ሁኔታ አረጋግጧል በሚል በሰነዱ ላይ የተመለከተውን ቀን ጋብቻው የተፈፀመበት ቀን ነው በሚል ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ይህንኑ ተቀብሏል፡፡

ይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶቹ የደረሱበት ድምዳሜ በተከራካሪ ወገኖቹ የቀረቡትን ማስረጃዎች ዓይነት እና ይዘት በመመርመር እና በመመዘን የተያዘ አቋም ነው፡፡ በህግ ስልጣን የተሰጣቸው የስር ፍርድ ቤቶች በዚህ መልኩ አጣርተው የደረሱበት ድምዳሜ በዚህ ሰበር ሰሚ ችሎት ሊለወጥ የሚችለው ውሳኔው በማስረጃ የተረጋገጠውን ፍሬ ነገር መሰረት ያላደረገ እንደሆነ፤ ወይም በማስረጃ ምዘና ረገድ መሰረታዊ የማስረጃ ምዘና መርህ ጥሰት ስለመፈፀሙ ሲረጋገጥ፤ ወይም ማስረጃዎቹ መሰረት ተደርጎ በተሰጠ የህግ ትርጉም ውስጥ የተፈፀመ መሰረታዊ የህግ አተረጓጎም ስህተት ሲኖር ስለመሆኑ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 80(3) እና በፌዴራል ፍርድ ቤቶች ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1234/2013 አንቀፅ 10 ለችሎቱ ከተሰጡት የዳኝነት ስልጣን መረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ አንፃር የቀረበው የሰበር አቤቱታ በስር ፍርድ ቤት የቀረቡት ማስረጃዎች እንዲመረመር እና በድጋሚ እንዲመዘን የሚጋብዝ የፍሬ ነገር ክርክር እንጂ የህግ ነጥብን የሚመለከት እንዳልሆነ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡ ሆኖም ችሎቱ በዚህ መልኩ ማስረጃን የሚመረምርበት እና የሚመዝንበት የህግ አግባብ ባለመኖሩ የአመልካች የሰበር አቤቱታ ውድቅ ተደርጎ ተከታዩ ውሳኔ ተሰጥቷል፡፡

ው ሳ ኔ

የፌዴራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት በመ/ቁ/216111 መጋቢት 20/2014 ዓ.ም በዋለው ችሎት የአመልካችን የይግባኝ አቤቱታ ውድቅ በማድረግ የሰጠው ትዕዛዝ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ህ/ቁጥር 348(1) መሰረት ፀንቷል፡፡

ት ዕ ዛ ዝ

1. የዚህን ሰበር ሰሚ ችሎት ክርክር ወጪ ግራ ቀኙ የየራሳቸውን ይቻሉ፡፡
2. በዚህ መዝገብ ላይ የተሰጠ የእግድ ትዕዛዝ ካለ ተነስቷል፡፡ ይፃፍ፡፡
3. መዝገቡ ተዘግቷል፡፡ ይመለስ፡፡

ማ ሲታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ት/በ

ማ ሰታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ሰነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም